በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ
ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር

# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከጃንዋሪ 1-10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከጃንዋሪ 11-20 እና ጃንዋሪ 21-31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጃንዋሪ 11/2023

አዲስ አበባ

ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ ........ - 1 -

ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ........ - 2 -

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 2 -

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት ........ - 3 -

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........ - 3 -

እ.ኤ.አ ከጀንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........ - 4 -

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 4 -

እ.ኤ.አ ከጀንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ.. - 5 -

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024........ - 5 -

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ........ - 5 -

እ.ኤ.አ ከጀንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር........ - 6 -

ሁኔታ ትንበያ ........ - 6 -

ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........ - 7 -

ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 7 -

እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ ........ - 8 -

ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31፣ 2024 ........ - 8 -

የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........ - 8 -

እ.ኤ.አ ከጀንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ - 9 -

እ.ኤ.አ ከጀንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ........ - 9 -




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ እና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለዉ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ነበራቸው፡፡ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአዲስ አበባ ቦሌ 0.8፣ በአርባ ምንጭ 9.4፣0.3 እና 1.7፤ በሀዋሳ 5.2፤ በደብረ ማርቆስ 0.6፤ በጅማ 14.9፤ በአማን 1.8፣2.6፣3.6፣47.8፣43.7 እና 3.7፤ በቦሬ 1.2፤ በጭራ 13.0 እና 2.1፤ በዲላ 0.2፤ በግዮን 0.5፤ በሆሳዕና 2.3፣1.2፤ በእምድብር 3.1፤ በሊሙገነት 6.8፤ በማጂ 19.2፤ በማሻ 40.2፣2.0 እና 20.0፤ በአዳማ 0.1፤ በሰኮሩ 2.2፣6.2፣ በሻምቡ 1.3፤ በቴፒ 11.5፣1.2 እና 8.6፤ በተርጫ 1.4፣3.5 እና 0.7 እንዲሁም በወራቤ 1.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል።


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት ማለትም ከኦሮሚያ ክልል ቦረና እና ጉጂ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች በብዙ ቦታዎቻቸዉ ላይ ከ20-103 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም ከኦሮሚያ ክልል አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ደቡብ ምዕራብ ሸዋ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ቄለም ወለጋ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ሀላባ፣ ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል ምስራቅ ጎጃም፤ከጋምቤላ ክልል የኢታንግ ልዩ ዞን፣ አኙአክ፣ ማዣንግ እና ኑዌር ዞኖች ላይ ከ0.5-20 በሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-2 ቀናት ያህል ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ስልጤ፣የየም ልዩ ዞን፣ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ጋሞ፣ባስኬቶ ዞኖች፤ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ቤንች ሸኮ፣የኮንታ ልዩ ዞን፤ከጋምቤላ ክልል ማዣንግ ዞን ላይ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ ነበራቸው (ካርታ 3) ፡፡




ስልክ +251115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

**በሌላ በኩል የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ፣ በሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ6 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ከ6 ዲ.ሴ በታች የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል ፡-**





**ምስል 1፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**





**ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ**



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት ብዛት





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጃንዋሪ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበር የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል የደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት ለጥቂት ቀናት አግኝተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ የነበረው እርጥበት የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የጎላ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡





ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ የአየር ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በጥቂት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ማለትም በላይኛውና በመካከለኛው ባሮአኮቦ እና መካከለኛው እና ታችኛው ኦሞ ጊቤ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 10/2024

ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመደበኛ ሁኔታ በጀንዋሪ ሁለኛዉ አሥር ቀናት በሰሜን ንፍቀ ክበብ ከሚገኘው ከሳይቤሪያ ከፍተኛ የአየር ግፊት ላይ በመነሳት ወደ ሀገራችን የሚገባው ደረቅና ቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ በሰሜን፣ በሰሜን ምስራቅና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ይስተዋላል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አንጻራዊ ጥንካሬ ይኖረዋል። በሌላ በኩል በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡


በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት በአሁኑ ጊዜ እየተስተዋለ የሚገኛዉ የበጋዉ ደረቅ፣ ፀኃያማ እና ነፋሻማዉ የአየር ሁኔታ በምስራቅ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሌላ በኩል በጃንዋሪ ሁለተኛዉ አስር ቀናት ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ላይ በመነሳት ወደ ሀገራች ከሚገባዉ እርጥበት አዘል አየር ሁኔታ በተለይም በደቡብና ደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው እንዲሁም በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ እርጥበት እና የደመና ሽፋን መጨመር እንደሚኖራቸዉ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በመካከለኛዉ፣ በሰሜን እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብና በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 7 )፡፡

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሁለተኛዉ አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ጉጂ፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ እንዲሁም ቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፣ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች እንዲሁም




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አብዛኛው ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የሚየገኙ ሲሆን፤ በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከአፋር ክልል ዞን 2፣ 4 እና 1፣ የምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ክልል ዞኖች፣ ከአማራ ክልል ማዕከላዊ፣ ሰሜን እና ደቡብ ጎንደር፣ ሰሜን እና ደቡብ ወሎ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ጎጀም፣ የአዊ ዞን እና ሰሜን ሸዋ ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ ጅማ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ(ሰላሌ)፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሸዋ፣ ባሌ እንዲሁም አዲስ አበባ ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ያገኛሉ (ካርታ 7)። በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናትም በጥቂት የሀገራችን የምስራቅ፣ የመካከለኛው እና የሰሜን ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚስተዋል አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 6)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ ዝቀተኛ የሙቀት መጠን




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከጃንዋሪ 11-20, 2024 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሚቀጥሉት የጃንዋሪ ሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት የበጋው ደረቅ፣ ፀሀያማና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ በምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ይስተዋላል፡፡ በሌላ በኩል በፀኃይ ኃይል ታግዞ ከሚፈጠሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በብዙ ቦታዎች ላይ ጠንካራ የደመና ሽፋን እንደሚኖር አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በተለይም በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛዉ፣ በሰሜን፣ በሰሜን ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ ሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ወቅቱን ያልጠበቀ ቀላል መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራቸዋል (ካርታ 8) ፡፡

Rainfall performance (mm) for 21-31 Jan 2024




ካርታ 8፡ እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21-31፣ 2024
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በጋ ሁለተኛው የዝናብ ወቅታቸው በሆኑትና ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም ለቋሚ ተክሎች፣ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የእንስሳት ልማትም ሆነ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ የሚኖረው እርጥበት የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ከፍኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 11 እስከ 20/2024 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በዉሀዉ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጪዎቹ አስር ቀናት የላይኛውና መካከለኛው አባይ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አሞ ጊቤ፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ እና ዋቢሸበሌ፤ በጥቂት የላይኛው አዋሽ እና አፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ያገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል ተከዜ፣ ኦጋዴን፣ አዋሽ፣ገናሌ ዳዋ፣ ላይ ደረቅና ከፊል ደረቅ እንደሚሆኑ ይጠበቃል፡፡



ስልክ +251 115538394 ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et